የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

**OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**

ሃያ ሦስተኛ ዓመት ቁጥር ፷፫
አዲስ አበባ ሐምሌ ፯ ቀን ፪ሺ፱ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

23nd Year No. 63
ADDIS ABABA, 14th July ,2017

**ማውጫ**

አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፴፩/፪ሺ፱ ዓ.ም

የጤናውን ዘርፍ ዘላቂ የልማት ግቦች ለማሳካት ለሚከናወነው በውጤት ላይ የተመሠረተ ፕሮግራም ማስፈፀሚያ የሚውል ተጨማሪ ብድር ከዓለም አቀፍ የልማት ማህበር ለማግኘት የተፈረመው የተጨማሪ ብድር ስምምነት ማፅደቂያ አዋጅ……………………………………………………..ገጽ ፱ሺ፯፻፬

**CONTENT**

Proclamation No. 1031/2017

International Development Association Financing Agreement for making available the Additional Financing for Health Sustainable Development Goals Program-for-Results Ratification Proclamation ……………..Page 9704

አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፴፩/፪ሺ፱

**በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥት እና በዓለም አቀፍ የልማት ማህበር መካከል የተደረገውን የብድር ስምምነት ለማፅደቅ የወጣ አዋጅ**

የጤናውን ዘርፍ ዘላቂ የልማት ግቦች ለማሳካት ለሚከናወነው በውጤት ላይ የተመሠረተ ፕሮግራም ማስፈፀሚያ የሚውል ፩፻፲ ሚሊዮን ፮፻ ሺ ኤስ.ዲ.አር (አንድ መቶ አስር ሚሊዮን ስድስት መቶ ሺ ኤስ.ዲ.አር) ተጨማሪ ብድር የሚያስገኘው ስምምነት በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥት እና በዓለም አቀፍ ልማት ማህበር መካከል ግንቦት ፲ ቀን ፪ሺ፱ ዓ.ም በአዲስ አበባ የተፈረመ በመሆኑ፤

ይህንኑ የብድር ስምምነት የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ሰኔ ፲፭ ቀን ፪ሺ፱ ዓ.ም ባደረገው ስብሰባ ያፀደቀው በመሆኑ፤

PROCLAMATION No. 1031/2017

**A PROCLAMATION TO RATIFY THE LOAN AGREEMENT BETWEEN THE GOVERNMENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA AND THE INTERNATIONAL DEVELOPMENT ASSOCIATION**

**WHEREAS**, a Financing Agreement, between the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the International Development Association stipulating that the International Development Association shall provide to the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia an additional Loan amount of 110,600,000 SDR (One hundred ten million six hundred thousand SDR ) for financing the Additional Financing for Health Sustainable Development Goals Program-for-Results in Addis Ababa on the 18th day of May 2017;

**WHEREAS**, the House of Peoples' Representatives of the Federal Democratic Republic of Ethiopia has ratified the said Loan Agreement at its session held on the 22nd day of June 2017;

**NOW,THEREFORE,** in accordance with Article 55(1) and (12) of the Constitution of the Federal Democratic

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ ፶፭(፩) እና (፲፪) መሠረት የሚከተለው ታውጇል፦

፩. <u>**አጭር ርዕስ**</u>

ይህ አዋጅ "የጤናውን ዘርፍ ዘላቂ የልማት ግቦች ለማሳካት ለሚከናወነው በውጤት ላይ የተመሠረተ ፕሮግራም ማስፈፀሚያ የሚውል ተጨማሪ ብድር ከዓለም አቀፍ የልማት ማህበር ለማግኘት የተፈረመው የተጨማሪ ብድር ስምምነት ማፅደቂያ አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፴፩/፪ሺ፱" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

፪. <u>**የስምምነቱ መፅደቅ**</u>

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥት እና በዓለም አቀፍ የልማት ማህበር መካከል ግንቦት ፲ ቀን ፪ሺ፱ ዓ.ም በአዲስ አበባ የተፈረመው ተጨማሪ ብድር ስምምነት ቁጥር 6090-ET በዚህ አዋጅ ፀድቋል፡፡

፫. <u>**የገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር ሥልጣን**</u>

የገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር በብድር ስምምነቱ የተገኘውን ፩፻፲ ሚሊዮን ፮፻ ሺ ኤስ.ዲ.አር (አንድ መቶ አስር ሚሊዮን ስድስት መቶ ሺ ኤስ.ዲ.አር) ተጨማሪ ብድር በብድር ስምምነቱ በተመለከቱት ሁኔታዎች መሠረት በሥራ ላይ እንዲውል ለማድረግ በዚህ አዋጅ ሥልጣን ተሰጥቶታል፡፡

፬. <u>**አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ**</u>

ይህ አዋጅ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።

**አዲስ አበባ ሐምሌ ፯ ቀን ፪ሺ፱ ዓ.ም**

**ዶ/ር ሙላቱ ተሾመ**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**

Republic of Ethiopia, it is hereby proclaimed as follows:

1. <u>**Short Title**</u>

This Proclamation may be cited as the "International Development Association Financing Agreement for making available the Additional Financing for Health Sustainable Development Goals Program for Results Ratification Proclamation No. 1031/2017".

2. <u>**Ratification of the Agreement**</u>

The Financing Agreement Number 6090-ET signed in Addis Ababa on the 18th day of May 2017 between the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the International Development Association is hereby ratified.

3. <u>**Power of the Ministry of Finance and Economic Cooperation**</u>

The Ministry of Finance and Economic Cooperation is hereby empowered to undertake all acts necessary for the utilization of the Loan amount of 110,600,000 SDR (One hundred ten million Six hundred thousand SDR ) in accordance with the terms and conditions set forth in the Financing Agreement.

4. <u>**Effective Date**</u>

This Proclamation shall enter into force on the date of publication in the Federal Negarit Gazette.

**Done at Addis Ababa, this 14th day of July,2017.**

**MULATU TESHOME (DR.)**

**PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**